# የስደተኞች ጉዳይ ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በሠው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ከትውልድ አገራቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች ጥገኝነትን በመስጠት ረዥም ታሪክ ያላት አገር ናት፡፡ ለአብነት ያህል በ7ኛው ክ/ዘመን ከዐረቢያ ተሰደው ለመጡ የነብዩ መሐመድ ተከታዮች፣ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ከአውሮፓ እና እስያ ተፈናቅለው ለመጡ ሰዎች እንዲሁም በፀረ-ቅኝ አገዛዝ እንቅስቃሴዎችና በእርስ በርስ ጦርነት፣ በፖለቲካ ቀውስና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ከተለያዩ የአፍሪካ አገራት ተሰደው ለመጡ ጥገኝነት ጠያቂዎች በሯን ክፍት በማድረግ ከለላ ስትሰጥ መቆየቷ ይታወቃል፡፡

በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ የሰዎች መፈናቀል ቀውስ አጋጥሟል፡፡ በመላው ዓለም የአገራትን ጥበቃና የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ድጋፍ የሚሹ ከ21.3 ሚሊየን በላይ ስደተኞች ይገኛሉ፡፡ ኢትዮጵያም ከ26 አገሮች የመጡ ከ930,000 የሚበልጡ ስደተኞችን ተቀብላ በማስተናገድ ከዓለምና ከአፍሪካ በቀዳሚዎች ተርታ ላይ ትገኛለች፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ከጎረቤት አገራት የመጡ የደቡብ ሱዳን፣ የሶማሊያ፣ የኤርትራ እና የሱዳን ስደተኞች ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ፡፡ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች በ27 መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ለሚገኙ ስደተኞች መንግስት ከተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊውን ሰብዓዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ መስከረም 20 ቀን 2016 ኒውዮርክ ላይ በተደረገው የመሪዎች ስብሰባ (Leaders' Summit) የስደተኞችን አያያዝ ለማሻሻል በዘጠኝ ጉዳዮች ላይ ቃል በመግባት አዲስ አቅጣጫ አስቀምጣለች፡፡ ይህ አቅጣጫ ስደተኞች በአገራችን በሚቆዩበት ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት ከኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች ጋር በማስተሳሰር ያላቸውን እውቀት፣ ክህሎትና አቅም እንዲጠቀሙ ብሎም ለአገራችን ልማት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ለስደተኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት መካከል በተቀናጀ መልኩ ለመስጠት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ምሉዕ ባለመሆኑና በስደተኞች አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለማረም በማስፈለጉ ሁሉን ያጠቃለለና ወጥ የሆነ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ እንደገና ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 2. የረቂቅ አዋጁ ዓላማዎች

የረቂቅ አዋጁ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በሥራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 409/1996 ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑና በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የስደተኞች ቁጥር በበቂ ሁኔታና ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለማስተናገድ እንዲቻል ማሻሻል በማስፈለጉ፤

- እ.ኤ.አ በ2016 በኒውዮርክ በተካሄደው የመሪዎች ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የስደተኞችን አያያዝ ለማሻሻል የገባውን ቃል (9 Pledges) ለመተግበር እንዲቻልና አገሪቱ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ለስደተኞች የተሰጡ መብቶችን ለመተግበር የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

- የተፈናቃዮች ቀውስ በዓለማችን እየተወሳሰበ፣ ወደ አገራችን የሚገቡ ስደተኞች ቁጥር እየጨመረ እና ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሚገኘው ድጋፍ እየቀነሰ በመምጣቱ ስደተኞችን በካምፕ አስጠልሎ ከመርዳት ባለፈ የአገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠንና በሚገኘው የውጭ ድጋፍ ከአገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ጋር በማስተሳሰር እንዲሁም ባላቸው አቅም ምርታማ ሆነው ራሳቸውን በመቻል የሚያጋጥሟቸውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በተቀናጀ መልኩ ለመፍታት መንግሥት የቀየሰውን አቅጣጫ ለማስተግበር የሚያስችል ሕግ በማስፈለጉ፤
- አገራችን ያለምንም መድሎ በሯን ክፍት በማድረግ ስደተኞችን በመቀበል በጸጥታ፣ በትምህርት፣ በጤናና መሰል አገልግሎቶች ለዓለም ተምሳሌት የሚሆኑ ስኬታማ ሥራዎችን እየሠራች የምትገኝ ቢሆንም በሥራ ላይ ያለው የሕግ ማዕቀፍ ይህንን ነባራዊ እውነታ የሚያንጸባርቅ ባለመሆኑ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 409/1996ን ማሻሻል በማፈለጉ ለቀረበው ረቂቅ አዋጅ ይህ የማብራሪያ ሠነድ ተዘጋጅቷል፡፡

### 3. ረቂቅ የስደተኞች ጉዳይ አዋጁ የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች

### ሀ. ለስደተኞች የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች

- መንግሥት በገባቸው ቃል ኪዳኖች መሰረት ስደተኞችንና ዜጎችን በጋራ ተጠቃሚ ለማድረግ በውጭ ድጋፍ በሚገነቡ የኢንደስትሪ ፓርኮችና በመስኖ የሰብል ምርት እንቅስቃሴ ውስጥ ስደተኞች ተሳታፊ መሆናቸው ራሳቸውን እንዲችሉና ምርታማ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል፡፡ በተጨማሪም ለውጭ ዜጎች በተፈቀዱ የሥራ መስኮች ላይ በቅጥር ስራም ይሁን በግል የስራ ዘርፍ እንዲሰማሩ መቻላቸው ከጥገኝነት ተላቀው ምርታማ እንዲሆኑና በአገሪቱ ልማት ላይ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ለስደት መንስኤያቸው ዘላቂ መፍትሔ እስኪያገኙ ድረስ የተረጋጋ ሕይወት እንዲኖራቸው ከማስቻሉም በላይ ወደ በለጸጉ አገራት ለመድረስ የሚያደርጉትን አደገኛ ጉዞ ይቀንሳል።
- ኢትዮጵያ በስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎችና በከተሞች ውስጥ ለሚገኙ ስደተኞች የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና የከፍተኛ የትምህርት ዕድል ትሰጣለች። ነገር ግን የስደተኞች የትምህርት ተሳትፎ ከአገሪቱ የትምህርት ተደራሽነት አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው። በመሆኑም የትምህርት ሽፋኑን ለማሳደግ መንግስት በገባው ቃል መሰረት የሕግ ማዕቀፉን ማሻሻሉ የስደተኞችን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተለይም የስደተኛ ሕፃናት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኙ መደረጉ የአገሪቱን ባሕል፣ ቋንቋና ታሪክ እንዲረዱ በማድረግ ከማህበረሰቡ ጋር ጥሩ መስተጋብር እንዲኖራቸው በማድረግ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ያጠናክራል፡፡ ከሕዳር 2000 ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት የተወሰኑ የኤርትራ ስደተኞችን ከካምፕ ውጭ እንዲኖሩ የሚያስችል የOCP ፖሊሲ ተግባራዊ ሲያደርግና ተጠቃሚ ሲያደርግ ቆይቷል። በመሆኑም መንግስት ይህንን ዕድል በማስፋት ከጠቅላላ ስደተኛው እስከ 10 በመቶ የሚሆኑ ሌሎች ስደተኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ቃል በመግባቱ በዚህ ረቂቅ አዋጅ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡
- መንግስት በገባቸው ቃል ኪዳኖች መሰረት ስደተኞች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረጉ ተጠቃሚነታቸውን ከፍ በማድረግ የተሻለ ህይወት እንዲኖሩ ያስችላል፡፡

### ለ. ለአገሪቱ ልማትና እድገት የሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች

ስደተኞችን በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ገድቦ ከማኖር ይልቅ ምርታማ እንዲሆኑና ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግና የአገሪቱን የልማትና የኢኮኖሚ እድገት ግቦች ለማሳካት የሚያግዝ ነው፡፡

ስደተኞችን በተመለከተ ከተቀመጡት እቅዶች መካከል ቀዳሚው ለስደተኞችና ለአገሪቱ ዜጎች በጋራ የሥራ ዕድል የሚፈጥር የኢንዱስትሪ መሠረተ-ልማት ግንባታ ማካሄድ ነው። ለዕቅዱም ተፈጻሚነት የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከፍተኛ ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ለአንድ መቶ ሺህ ሰዎች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታዎችን ለማካሄድ ከተ.መ.ድ፣ ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ፣ ከዓለም ባንክ እና ከሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በትብብር ለመስራት ታቅዷል። እነዚህ ፓርኮች ሥራ ሲጀምሩ በሚፈጥሩት የሥራ ዕድል 70% ኢትዮጵያውያን 30% ደግሞ ስደተኞች ተጠቃሚ ይሆናሉ። የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ግንባታ የስራ እድል ከመፍጠር፣ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘትና የካፒታል እጥረትን በመቅረፍ የኢንደስትሪ ልማትን እንደሚያፋጥን ይታመናል፡፡ ሌላው ለመስኖ ሥራ የሚሆን 10,000 ሄክታር መሬት አዘጋጅቶ ኢትዮጵያውያንና ስደተኞች በጋራ ሰብል በማምረት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ የተያዘው ዕቅድ ነው። በዕቅዱ መሠረት እስከ 100,000 ሰዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ። ዕቅዱ እንዲሳካም ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የገንዘብ ተቋማት የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ።

ስደተኞችንና የአካባቢውን ነዋሪ የሚጠቅሙ የልማት ፕሮጀክቶች የሁለቱንም ማኅበረሰቦች የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ከመርዳቱ በተጨማሪ በስደተኞችና በአካባቢው ነዋሪ መካከል በውሱን የተፈጥሮ ሐብት ሽሚያ ሊነሱ የሚችሉ አለመግባባቶችን እና ግጭቶችን በመቀነስ የአካባቢውን ሰላም ከማስጠበቅ አንጻርም ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

## ሐ. ረቂቅ አዋጁ ከውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች አንጻር ያለው ፋይዳ

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍንና በጦርነት ምክንያት የሚፈጠር ሰብዓዊ ቀውስ እንዲቆም ከምታደርገው ያላሰለሰ ጥረት በተጨማሪ ከተለያዩ አገራት የሚመጡ ስደተኞችን ተቀብላ እያስተናገደች ትገኛለች። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከጎረቤት አገሮች ሕዝቦች ጋር የተሳሰሩ በመሆናቸው በስደት ላይ ያሉ የእነዚህን ሕዝቦች ሕይወት ለማሻሻልና የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን በማጠናከር ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲኖር ይረዳል። ይህንን የሚያንፀባርቅ የሕግ ማዕቀፍ መኖሩ አገሪቷ ላስቀመጠችው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራቴጂ መሳካት አስተዋጽዖ ያበረክታል፡፡

## 4. የሕጉ የዝግጅት ሂደት

የረቂቅ አዋጁ ዝግጅት ከአንድ ዓመት በላይ የፈጀ ሲሆን ተጠናቆ እስከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ የሚከተሉት ዓበይት ክንውኖች ተካሂደዋል፡፡

### 4.1 በስደተኞች አስተዳደር፣ በአገልግሎት አሰጣጥና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ያሉ ችግሮችን መለየትና መረጃ ማሰባሰብ

በኢትዮጵያ የስደተኞች አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በተመለከተ (ለምሳሌ በስደተኞች ሁለተኛ ፍልሰት፣ በስደተኞች መተዳደሪያ ደንብ፣ በከተማ ስደተኝነት ወዘተ) የዳሰሳ ጥናት ትደርጓል፡፡ በተጨማሪም በስደተኞች ጉዳይ አስተዳደር እና የተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር የመረጃ ቋት ላይ የተገኙ መረጃዎችንና በየዓመቱ ከስደተኞች ጋር ከተደረጉ አሳታፊ የዳሰሳ ጥናቶችን በማሰባሰብ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችና የአሰራር ክፍተቶችን ለመለየት ጥረት ተደርጓል፡፡ ለረቂቅ ሕጉ ዝግጅት የሚረዱ በርካታ ሰነዶችን፣ ስታቲስቲካል መረጃዎችን፣ አለም አቀፍ መመዘኛዎችን (standards) እንዲሁም የተለያዩ አገራት ተሞክሮዎችና ሕጎችን በማሰባሰብና በመመርመር ግብዓት ተወስዷል፡፡

### 4.2 በስራ ላይ ያሉ የአገሪቱ ሕጎች ያሉባቸውን ክፍተቶች መለየት

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ 409/1996 ስደተኞችንና ጥገኝነት ጠያቂዎችን በተመለከተ ከስደተኝነት እውቅና አሰጣጥ ጀምሮ ዘላቂ መፍትሔ እስከመፈለግ ባለው ሂደት ውስጥ የስደተኞች መብቶችና ግዴታዎች ዙሪያ ድንጋጌዎች አሉት፡፡ ሆኖም ድንጋጌዎቹ ግልጽ በሆነ አኳኋን ተዘርዝረው ባለመቀመጣቸው፣ ያልተካተቱ ሃሳቦች በመኖራቸውና በርካታ ክፍተቶች ያሉት በመሆኑና የስደተኞችን መብቶችና ግዴታዎች የሚመለከቱት አንቀጾች አቀማመጥ ጠቅለል ብለው የተቀመጡ በመሆኑ ለአገልግሎት ሰጪ አካላት አተገባበር አስቸጋሪ የነበሩ ክፍተቶች በዚህ ረቂቅ አዋጅ እንዲስተካከሉ ተደርጓል፡፡

### 4.3 የአለም አቀፍ መመዘኛዎችንና ተሞክሮዎችን መመርመር

የስደተኞች ችግር የተቀባይ ወይም መነሻ አገር ችግር ብቻ ሳይሆን የአለም አቀፍ ማህበረሰብ የጋራ ግዴታ ነው፡፡ የስደተኞች ከለላ በአለም አቀፋዊ ትብበርና ወንድማማችነት መንፈስ እንደየአገራቱ አቅም የሚተገበር ሲሆን አፈጻጸሙም በአለም አቀፍና አህጉራዊ የስደተኞች ስምምነቶች የሕግ ማዕቀፍ የሚገዛ ነው፡፡ አለም አቀፍ ደረጃዎች (international standards) እና የሌሎች አገራት ተሞክሮ (best practices) በመውሰድ እንደአገራችን ነባራዊ ሁኔታ አጣጥሞ በመውሰድ ለረቂቅ ሕጉ ግብዓትነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም ረቂቅ የስደተኞች ጉዳይ አዋጁ ይዘት አለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የ1951 (እ.ኤ.አ) የስደተኞች ኮንቬንሽንና ተዛማጅ የሆነው የ1967 (እ.ኤ.አ) ፕሮቶኮል፣ የ1969 (እ.ኤ.አ) የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽንና ሌሎች ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የሰብአዊ መብት ሰነዶችን በመመርመር የተለዩት ክፍተቶች እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ጋር በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም በስደተኛ ብዛት፣ ስነ-ሕዝብ ስብጥርና በመሳሰሉት መለኪያዎች ተቀራራቢ ሁኔታ ላይ ያሉ ሃገራት ተሞክሮዎችና ሕጎች ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሰረት የኡጋንዳ የስደተኞች ሕግ፣ የዛምቢያ የስደተኞች ቁጥጥር ሕግ፣ የደቡብ አፍሪካ የስደተኞች ሕግ እና የኬንያ የስደተኞች ሕግ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በመመርመር ለረቂቅ አዋጁ ግብአት እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

ኡጋንዳ በአፍሪካ የተሻለ የስደተኞች አጠባበቅና አስተዳደር ያላትና ሰፋ ያሉ መብቶችን የያዙ ሕጎች ያሏት በመሆኑና በምትቀበለው የስደተኞች ብዛት ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢ መሆኑ ግንዛቤ ላይ ስለተደረሰ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎች በዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር አስተባባሪነት ከጥር 14 እስከ 19 ቀን 2009 ዓ.ም ወደ ኡጋንዳ በመሄድ ጥናታዊ ጉብኝት አካሂደዋል፡፡ በጉብኝቱም ኡጋንዳ 35 ሚሊዮን ከሆነው የህዝብ ብዛቷ አንጻር ከ1 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ስደተኞችን (10% የሚሆኑት በከተሞች ይኖራሉ) ተቀብላ የምታስተናግድና ያለገደብ የመንቀሳቀስ፣ የመስራት፣ በንግድ የመሳተፍ፣ የባንክ ሂሳብ የመክፈት፣ ትምህርትና ጤና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን በማግኘት በስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ ሳይወሰኑ ራሳቸውን ችለው ለአገሪቱ ልማት አስተዋጽኦ እያበረከቱ እንደሚገኝ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህን ተሞክሮ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በማጣጣም ለረቂቅ አዋጁ ግብአትነት ውሏል፡፡

### 4.4 ባለድርሻ አካላትን ማወያየት

ረቂቅ ሕጉን ለማዳበር ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚከተሉት የምክክር መድረኮች ተደርገዋል፡፡

- ሐምሌ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በሌሎች አገራት ተሞክሮዎችና ሕጎች ዙሪያ ከተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ኤክስፐርቶች ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡

- ነሐሴ 5 ቀን 2008 ዓ.ም ከተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ኤክስፐርቶች ጋር በረቂቅ ሕጉ ዙሪያ ለሁለተኛ ጊዜ ምክክር ተደርጓል፡፡

- የፌደራል መንግስት መስሪያቤቶች፣ አ.አ ዩኒቨርሲቲና የሕግ ምርምር ተቋማት ተወካዮች ጋር የካቲት 20 ቀን 2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ኢ.ሊ.ሊ. ሆቴል ምክክር ተደርጓል፡፡ በዚህ ምክክር ወቅት ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ከፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ ባንክ፣ ከኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ፣ ከፌደራል ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ኤጀንሲ፣ ከፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ተቋም፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ተወካዮች በወቅቱ በረቂቅ ደንብ ደረጃ ተዘጋጅቶ በነበረው ሕግ ላይ ውይይት በማድረግ ጠቃሚ የሆነ ግብአት የተገኘ ሲሆን በውይይቱ ወቅት ከተሳታፊዎች በተገኘው አስተያየት መሰረት ረቂቅ ደንቡ ወደ ረቂቅ አዋጅ እንዲቀየር ተደርጓል፡፡ በውይይቱ ወቅት ስደተኞች ስላላቸው ልዩ ሁኔታና ከዜጎች በላይ ለጥቃት የተጋለጡ መሆናቸውን እንዲሁም በረቂቅ ሕጉ ላይ የተቀመጡ መብቶች በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ድጋፍ ጭምር የሚተገበሩ መሆናቸውን በመወያየት መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ከውይይቱ በኋላም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ፣ ከፍትሕና ሕግ ሥርዓት ምርምር ተቋም እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የሁለትዮሽ ምክክር በማድረግና ተጨማሪ አስተያየቶችን በጽሑፍ በመቀበል ረቂቅ አዋጁ እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ በጎንዮሽም ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ተወካዮች፣ ከለጋሽ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሌሎች አካላት ጋር በተለያየ ጊዜ በረቂቅ ሕጉ ላይ ምክክሮች ተደርገዋል፡፡

- የተሰጡት አስተያየቶችን በማካተት ሕጉን የማበልጸግ ስራ ከጠቅላይ አቃቤ ህግ ጋር በመሆን ተሰርቷል፡፡ በሂደቱም በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ላይ ያሉ ድንጋጌዎች ጠቅለል ያሉና ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታና የሕግ ሥርዓት አንጻር የተቃኙ ባለመሆናቸው እንዲሁም በስደተኞች ዙሪያ እየተሰሩ ያሉ ሰፊ ስራዎችን ለማስፈጸም የሚረዳ በመሆኑ ዘርዘር በማድረግ በረቂቅ አዋጁ እንዲካተቱ ሆኗል፡፡

## 5. የረቂቅ አዋጁ ይዘት

ረቂቅ አዋጁ በሥራ ላይ ያለው የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 409/1996 ውስጥ ያሉ አንቀጾችን በማካተት አንዳንድ አንቀጾችን በማሻሻል፣ የተወሰኑትን በመሰረዝ እና አዲስ አንቀጾችን በመጨመር እንዲሁም በስደተኞች መብትና ግዴታ ዙሪያ የተጨመሩ ወይም የተስተካከሉ ዝርዝር አንቀጾች ተዘጋጅቷል፡፡ የተሻሻሉት፣ የተሰረዙት፣ በአዲስ የተተኩትና የተጨመሩት አንቀጾች ብዛት ያላቸው በመሆኑ ለአጠቃቀም በሚያመችና ወጥ በሆነ መልኩ እንዲዘጋጅ የተደረገ ሲሆን፣ በረቂቅ አዋጁ የተጨመሩና የተስተካከሉ አንቀፆች እንደሚከተለው ተብራርተዋል፡፡

### 5.1 ጠቅላላ

በአዋጁ አንቀጽ 2(1) ላይ "ባለሥልጣን" በማለት ትርጉም ተሰጥቶት የነበረው የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን በአሁኑ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 804/2005 አንቀጽ 4(1) መሰረት እንደገና የተቋቋመው የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በመሆኑ በረቂቅ አዋጁ ውስጥ "አገልግሎት" በሚል ትርጉም ተሻሽሎ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

"የቤተሰብ አባል" ትርጉም ተቃራኒ ፆታ ያላቸው የስደተኛው ባል ወይም ሚስት እና ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነ ያላገባ የስደተኛው ልጅ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የስደተኞችን ልዩ ሁኔታ፣

የመጡበትን አገር ባሕል እንዲሁም በመሃከላቸው ያለውን ቅርርብ (dependency) ከግምት ውስጥ በማስገባት በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 2(9) አገልግሎቱ "የቤተሰብ አባል" ሆነው ሊቆጠሩ የሚችሉ በማጣራት እንዲያካትት ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡

## 5.2 ጠቅላላ መርሆዎች

### የስደተኝነት መስፈርት

በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ 409/1996 አንቀጽ 4(3) የተቀመጠው የስደተኝነት መስፈርት ተፈጻሚነቱ ከአፍሪካ አገራት ለሚመጡ ስደተኞች ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ ያፀደቀችው የ1969 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች ኮንቬንሽን በአንቀጽ 1(2) የአዋጁ ተፈጻሚነት ከአፍሪካ አገራት ለሚመጡ ስደተኞች የተገደበ ሳይሆን ከማንኛውም አገር ለሚመጡ ስደተኞችም ጭምር ተፈጻሚ ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱን ህጎች ማስታረቅ አስፈላጊ በመሆኑ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ውጭ በዋናነት ከየመን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስደተኞች የቡድን እውቅና የሚሰጥበት አካሄድ በመኖሩ የኮንቬንሽኑ ትርጉም ተወስዶ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 4፣ 5 እና 20 ላይ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

### ከአገር መውጣት በኋላ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ስለሚሰጥ የስደተኝነት ዕውቅና

ሰዎች ለሌላ ጉዳይ ከአገራቸው ወጥተው ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ በትውልድ አገራቸው ወይም በቀድሞ መደበኛ የመኖሪያ ሥፍራቸው በሚፈጠሩ ክስተቶች ወደአገራቸው ቢመለሱ ተጨባጭ አደጋ የሚደርስባቸው ከሆነ የስደተኝነት ዕውቅና የሚያገኙበት አግባብ የዓለም አቀፍ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 5 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

### የስደተኝነት ዕውቅናን ስለመሠረዝና ስለመሻር

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ያሉት የስደተኝነት ዕውቅና መሠረዝ እና መሻር በስደተኞች ሕግ መርሕና በስደተኞች ኮንቬንሽኖች መሰረት ጽንሰ ሃሳቦቹ ተለይተው በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 7 እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡ የስደተኝነት ዕውቅናው የተሰረዘበት ወይም የተሻረበት ሰው ይግባኝ የማቅረቢያ ጊዜ ወደ 60 ቀናት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

### እንደስደተኛ መቆጠር ስለሚያበቃበት ሁኔታ

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 8 ላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች እንደ ስደተኛ መቆጠር በሚያበቃበት ወቅት በአገልግሎቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ስደተኛ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አቤቱታውን ስለሚያቀርብበት ሁኔታ ያልተገለጸ በመሆኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 8 ስር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

### የቤተሰብ አንድነት

አዋጁ በኢትዮጵያ ውስጥ በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚኖሩ የስደተኞች ወይም የጥገኝነት ጠያቂዎች ቤተሰብ አባላት አንድ ላይ ለመሆን ሲጠይቁ ከስደተኞች አንድነት መርኅ (principle of family unity) አንጻር አብረው የሚኖሩበትን ሁኔታ አገልግሎቱ እንደሚያመቻች በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 13 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## 5.3 የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን ሥነ-ሥርዓት

### የስደተኝነት እውቅና እንዲሰጥ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 13(1) ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየት የፈለገ ማንኛውም ሰው በ15 ቀናት ውስጥ ማመልከት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህ ጊዜ በቂ ባለመሆኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 14 ወደ 30 ቀናት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

### በአገልግሎቱ ስለሚሰጥ ውሳኔ

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 14 አገልግሎቱ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጥ የሚቀርብን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ አይገልጽም፡፡ በመሆኑም በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15(1) አገልግሎቱ በ6 ወራት ውስጥ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት ተካቷል፡፡ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15(2)(ሠ) አገልግሎቱ የስደተኝነት ዕውቅና እንዲሰጥ የቀረበለን ማመልከቻ በሚመረምርበት ወቅት የጥገኝነት ጠያቂው የፆታ ምርጫና ከወላጅ እና አሳዳሪ የተለየ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ልዩ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርበት ተቀምጧል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 14(3) በአገልግሎቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ይግባኝ ለማቅረብ የተቀመጠው የ30 ቀናት ገደብ በቂ ባለመሆኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15(4) ወደ 60 ቀን ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

### የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አባላት

በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 16(1) የይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አባልነት ተወካይ መስሪያ ቤቶች መካከል የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ወደ ፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር እንዲሁም የፍትህ ሚኒስቴር ወደ ፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የስም ለውጥ አድርገዋል፡፡ ይህም ለውጥ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 17 እንዲንጸባረቅ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም የተወካዮቹ ስብጥር በተመለከተ ለውጦች የተደረጉ ሲሆን በተጨማሪነት ከፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን አንድ ተወካይ እንዲኖር ተደርጎ ተሻሽሏል፡፡

### የይግባኝ ሰሚ ጉባዔው ስልጣንና ተግባር

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 17 የይግባኝ ሰሚ ጉባዔው በአዋጁ መሰረት የሚቀርብለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ባለመደንገጉ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 18(1) በሶስት ወራት ውስጥ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት ተቀምጧል፡፡

### የቡድን የስደተኝነት ዕውቅና ስለመስጠት

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ከደቡብ ሱዳን፣ ሱማሊያ፣ ኤርትራና የመን ለመጡ ስደተኞች የቡድን ዕውቅና እየሰጠች ትገኛለች፡፡ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 19 የአገልግሎቱ ኃላፊ በአንቀጽ 4(3) የተደነገገውን የሚያሟሉ የሰዎች ቡድን ስደተኛ ናቸው ብሎ መወሰን እንደሚችል ይገልጻል፡፡ ሆኖም ይህን በሚወስንበት ወቅት የአሰጣጡ ሂደት፣ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፣ ውሳኔው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ፣ ውሳኔው የሚያበቃበት ጊዜና ሁኔታ በተመለከተ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 20 እነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች ተብራርተው እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

## 5.4 መብቶችና ግዴታዎች

### ትምህርት ማግኘት

በአዋጁ አንቀፅ 21(3) መሠረት ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች ትምህርትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት የኢትዮጵያ ዜጎች ላልሆኑ ሰዎች በተሰጡ መብቶች እንደሚጠቀሙ፤ በተጣሉባቸው ግዴታዎችም እንደሚገዙ ይደነግጋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በኒውዮርክ የመሪዎች ጉባዔ ላይ ከገባቸው ቃል ኪዳኖች ውስጥ አንዱ የሃገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን እና ያለምንም መድልዎ ለሁሉም ስደተኞች የትምህርት ተደራሽነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም ኢትዮጵያ ለማሳካት እየሠራች ካለችው የዘላቂ ልማት ግቦች (SDG) ዓላማዎች ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ ይህንንም ለመተግበር በአዋጁ አንቀጽ 21(3) ስር ያለውን ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 23 ላይ ማንኛውም ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ የሚሆንበትን አግባብ በዝርዝር ደንግጓል፡፡ ስለሆነም ስደተኞች የቅድመ-መደበኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ እንደ ኢትዮጵያ ዜጎች ያክል ተጠቃሚ ሲሆኑ፣

በሌሎች የትምህርት ደረጃዎችና ዘርፎች ላይ የአገር አቅም በሚፈቅደው መጠን እንደውጭ ዜጋ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ይህም ከአገሪቷ ፖሊሲ ጋር የሚሄድና በትምህርት ረገድ ለስደተኞች የሚደረግን ድጋፍ ያመለክታል፡፡

### የመስራት መብት

በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀፅ 21(3) ስደተኞች ኢትዮጵያውያን ላልሆኑ ሰዎች በተሰጡ የስራ መስኮች ላይ መሰማራት እንደሚችሉ ደንግጓል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በኒውዮርክ የመሪዎች ጉባኤ ከገባቸው ቃል ኪዳኖች ውስጥ አንዱ ስደተኞች በተለያዩ የስራ መስኮች ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 25 ስደተኞች የቅጥር ሥራን በተመለከተ ለውጭ ሃገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች እጅግ የተሻለውን ያክል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ፣ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት እንደ እርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ አነስተኛና ጥቃቅን፣ እደጥበባትና የንግድ ዘርፎች ውስጥ በግል ለመሰማራትና የኢንዱስትሪና የንግድ ማኅበሮችን ለማቋቋም የኢትዮጵያ ዜጎች ላልሆኑ ሰዎች ከተሰጡ መብቶች እጅግ የተሻለውን ያክል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በፕሮፌሽናል ስራ ለውጭ አገር ዜጎች በተፈቀዱ መስኮች ውስጥ መሰማራት እንደሚችሉና በሚሰሩበትም ወቅት ከዜጎች መድልዎ ሳይደረግባቸው አግባብ በሆኑ እንደ ታክስ፣ የአሠሪና ሰራተኛ ወዘተ በመሳሰሉ ሕጎች እንደሚገዙ ይደነግጋገል፡፡ በተጨማሪም ዜጎችንና ስደተኞችን በጋራ ተጠቃሚ ለማድረግ በተቀረፁ ገቢ ማስገኛ ልዩ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተቀጥረው መስራት እንደሚችሉ ተካቷል፡፡ የቅጥር ሥራን አስመልክቶ በውጭ አገር ዜጎች ላይ የተጣሉ ክልከላዎች ኢትዮጵያዊ ሚስት/ባል ባገባ፣ ወይም አንድ ወይም ከአንድ በላይ የኢትዮጵያ ዜግነት የያዘ ልጅ ያለው ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ ላይ ተፈጻሚነት እንዳይኖራቸው ተደርጓል፡፡

### የመደራጀት መብት

በስደተኞች ኮንቬንሽኖች ለስደተኞች ከተሰጡ መብቶች ውስጥ አንዱ የመደራጀት መብት ነው፡፡ ነገር ግን በሥራ ላይ ያለው የመደራጀት ሕግ በፌዴራል የበጎ አድራጎትና ማሕበራት ኤጀንሲ እንዲሁም በተለያዩ የሴክተር መሥሪያቤቶች አማካይነት የሚፈፀም ሲሆን ይህም ሕግ ስደተኞች እንዲደራጁ የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ስለሆነም በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 26 ላይ ዕውቅና ያገኙ ስደተኞች ከፖለቲካ ነፃ በሆኑና ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች እንዲሁም የሠራተኛ ማኅበራት የመደራጀት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡

### የመዘዋወር ነፃነት

የመዘዋወር ነጻነት ራሱ ሰብአዊ መብት ከመሆኑም ባሻገር ስደተኞች በሌሎች መብቶቻቸው መጠቀም እንዲችሉ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም በስደተኞች ኮንቬንሽኖች ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ሆኖም ይህ መብት በስደተኞች አዋጅ ላይ በግልጽ ያልተጠቀሰ በመሆኑ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታና ስደተኞች በመጠለያ ጣቢያ የሚቀዩበትን እንዲሁም ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር የሚፈቀድላቸውን (Out of camp policy) አሰራር ግምት ውስጥ በማስገባት ለአተገባበር በሚመች መልኩ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 27 ላይ ተካቷል፡፡

### ንብረት የማፍራትና የማስተላለፍ መብት

ስደተኞች የስራ ፈቃድ አግኝተው ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉ ለማስቻልና ይህንን ለመተግበር እንዲቻል የሥራቸው ፍሬ የሆኑ ንብረቶች የሕግ ዋስትና እንዲያገኙ መደንገግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 28 ንብረት ማፍራትና ማስተላለፍ በተመለከተ ለውጭ ሃገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች እጅግ የተሻለውን ያክል ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ ኢትዮጵያ በመጀመሪያ ጊዜ በሚገቡበት ጊዜ ይዘውት የመጡት ሀብትና ንብረት ያለ ቀረጥ እንዲያስገቡ እንዲሁም አግባብ ያላቸው ሕጎች

እንደተጠበቁ ሆነው ወደ መጡበት አገር ሲመለሱ ወይም ወደ ሶስተኛ አገር በሚወጡበት ጊዜ ይዘው የመጣጡትን ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ያፈሩትን ሁብትና ንብረት ይዘው እንዲወጡ እንዲፈቀድላቸው ተደርጓል፡፡ የአእምሮአዊ ንብረት በሚመለከትም ለኢትዮጵያ ዜጎች የሚደረገውን ያክል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## ፍትህ የማግኘት መብት

በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ማንኛውም ሰው ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ እንዲሁም በ1951 የስደተኞች ኮንቬንሽን አንቀጽ 16 ስር ፍትህ የማግኘት መብት ተቀምጧል፡፡ ሆኖም ይህ መብት በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ በግልጽ ያልተቀመጠ በመሆኑና በዚህም የተነሳ ስደተኞች በተግባር ብዙ ችግሮች እያጋጠሟቸው በመሆኑ ይህንን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 29 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ

የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ የማግኘት መብትን አስመልክቶ በግልፅ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማገኘት የሚያስፈልጉት መስፈርቶች የስደተኞችን ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገቡ ባለመሆኑና የስደተኞችን የመታወቂያ ሰነድ በመጠቀም ለማግኘት የማያስችል በመሆኑ እንዲስተካከሉ አስፈልጓል፡፡ በዚህም መሠረት በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 30 ስደተኞች የኢትዮጵያን መንጃ ፈቃድ ለማግኘት የሚችሉበትን አግባብ አካቷል፡፡

## የባንክ አገልግሎት

ስደተኞች በአዋጁ በተለያዩ የስራ መስኮች ሲሳተፉ የሚያገኙትን ገቢ ለማስቀመጥም ሆነ ለማውጣት እንዲችሉ የባንክ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ሁኔታ በሌሎች ሕጎች በግልጽ ያልተቀመጠ በመሆኑና በባንኮች መካከል ወጥ የሆነ አሰራር ስለሌለ በረቂቅ አዋጁ ስደተኞች የሚሰጣቸውን የመታወቂያ ሰነድ በመጠቀም የባንክ ሂሳብ ደብተር የመክፈት፣ ገንዘብ የማስቀመጥ፣ የማውጣት፣ የማስተላለፍ፣ የመሳሰሉ አገልግሎቶች ሊያገኙ የሚችሉበትን አግባብ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 32 ላይ ተደንግጓል፡፡

## የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት

ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ቀደም ሲል በኢትዮጵያውያን ስም የተንቀሳቃሽ ስልክ አገልግሎት እየተጠቀሙ ስለነበር ለቁጥጥር የማይመች ሁኔታ ነበር፡፡ ስለሆነም በአገልግሎቱ የሚሰጣቸውን መታወቂያ በመጠቀም በስማቸው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበትን አግባብ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 33 ላይ ተደንግጓል፡፡

## ራሽን ስለማግኘት

በስደተኞች ኮንቬንሽን አንቀጽ 20 ስር የራሽን ስርዓት በሚተገበርበት ወቅትና የምርቶች አቅርቦት እጥረት ተፈጥሮ ለዜጎች ራሽን በሚከፋፈልበት ወቅት አገሮች ስደተኞችን እንደዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በአገራችንም እንደ ስኳር፣ ዘይት ወዘተ የመሳሰሉ ምርቶች በእጥረት ምክንያት በራሽን መልክ በሚከፋፈልበት ጊዜ ስደተኞች መጠቀም ባለመቻላቸው በኮንቬንሽኑ መሠረት ከዜጎች ጋር በተመሣሣይ ሁኔታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 34 ላይ ተካቷል፡፡

**ክፍያዎችን በተመለከተ**

አብዛኞቹ ስደተኞች በአገልግሎቱና በአጋር ድርጅቶች በሚሰጡ እርዳታዎች የሚተዳደሩ በመሆኑና ገቢ የሌላቸው ስለሆነ እንዲሁም በስደተኞች ኮንቬንሽን ክፍያዎችን በተመለከተ በዜጎች ላይ ከሚጣለው በላይ ስደተኞች ላይ እንደማይጣል ስለሚደነግግና መድልዎ እንዳይደርስባቸው ለመከላከል የሚያስችል ድንጋጌ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 36 ላይ ተካቷል፡፡

**ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ስለሚደረግ ልዩ ጥበቃ**

የስደተኞች አዋጅ አንቀጽ 22 ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ስደተኛ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አረጋዊያን፣ የአካል ጉዳተኞች እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ ቡድኖች ልዩ ጥበቃ መደረግ እንዳለበት ጠቅለል ባለ መልኩ ይደነግጋል፡፡ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 37 እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ስደተኛ ሴቶችና ህጻናትን አገልግሎቱ ከጥቃት የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለበት በመጨመር ዘርዘር ባለ መልኩ ተካቷል፡፡

**እውቅና ያገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ግዴታዎች**

የአዋጁ አንቀጽ 20 እና 21 የስደተኞችና የጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶችና ግዴታዎችን ጠቅለል በማድረግ ያስቀምጣል፡፡ ነገር ግን ጠቅለል ያለ በመሆኑ ከአገልግሎቱ ጋር የመተባበርና በተጠየቁ ጊዜ መረጃ የመስጠት ግዴታን በመጨመር ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች የአገሪቱን ሕጎች ማክበርና ከሚኖሩበት አካባቢ ባህል፣ መልካም አኗኗርና የሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆኑ ተግባራት መቆጠብ እንዳለባቸው በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 38 ላይ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

**ከዜጎች ጋር ስለማዋሃድ በሚመለከት**

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 40 ላይ እንደተጠቀሰው ለረጅም ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩ ስደተኞች በተናጠልም ሆነ በቡድን ከአገሪቱ ዜጎች ጋር ተዋህደው የሚኖሩበትን ሁኔታ አገልግሎቱ ሊያመቻች እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ከዜጎች ጋር ተዋህዶ መኖር ለስደተኞች ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ከሚባሉት ውስጥ አንደኛው ሲሆን የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌ ኢትዮጵያ በመሪዎች ጉባዔ ላይ ከ20 አመት በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የቆዩ ስደተኞች ከዜጎች ጋር ተዋህደው ራሳቸውን ችለው እንዲኖሩ እንደምትፈቅድ ከገባችው ቃል ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ አገራት ይህንን መፍትሔ በተለያየ መልኩ ማለትም ስደተኞች እንደዜጎች ሰርተው ለመኖር ፈቃድ መስጠት ጀምሮ የመኖሪያ ፈቃድ መስጠትና ቀስ በቀስ ዜግነት እስከመስጠት ድረስ ይተገብሩታል፡፡ ይህ አንቀጽ ጠቅለል ባለ መልኩ የተቀመጠ ሲሆን ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ዝርዝር አተገባበሩ ለወደፊት በደንብ/በመመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**ማጠቃለያ**

የኢትዮጵያ መንግሥት በኒውዮርክ የመሪዎች ጉባኤ በገባቸው ቃል ኪዳኖች መሠረት ስደተኞችን ከአገሪቱ ዘላቂ የልማት ስትራቴጂ ጋር በማስተሳሰር፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማጠናከርና በማስፋፋት ስደተኞችንና ዜጎችን በጋራ ተጠቃሚ የሚያደርግ አቅጣጫ በመከተል ላይ ይገኛል፡፡ ረቂቅ አዋጁ ይህንን አቅጣጫ ለመተግበር አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ እንዲሁም ረቂቅ አዋጁ የስደተኝነት ዕውቅና አሰጣጥንና የስደተኞችና የጥገኝነት ጠያቂዎች መብቶችና ግዴታዎችን በተመለከተ በሥራ ላይ ባለው አዋጅ ላይ የሚታዩትን ክፍተቶች የሚሞላና በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የጥገኝነት ጠያቂ ቁጥር በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድ እንዲቻል ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡